4127 Redwood
Oakland, CA 94619
(510) 530-3681

No: 3012/10
Date: 11/05/2010

# ሠላሳኛው የሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ መደበኛ ስብሰባ መግለጫ

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሠላሳኛ መደበኛ ጉባኤውን በኦሀዮ ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ካቴድራል ከጥቅምት ፳፬ - ፳፮ ቀን ፪ ሺ ፫ ዓ.ም. አካሂዷል። ቅዱስ ሲኖዶሱ በጉባኤው ላይ የቤተ ክርስቲያናችንን አጠቃላይ ወቅታዊ ማኅበራዊ መንፈሳዊ ሁኔታዎች በዝርዝርና በጥልቀት በመወያየት የሚከተለውን መግለጫ አውጥቶአል።

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሀገር አንድነት ለሕዝብ ነጻነት እና ዕውቀት መሠረት ናት። በመሆኑም በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ለኢትዮጵያውን መሰባሰብ ዋስትና ሆና አሁንም ሕዝቡን በአንድ ዓላማ እንዲቆም በማድረግ ላይ ነች። ይህም የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት፥ ሕዝቡን በነጻነቱና በእምነቱ እንዲተማመን አድርጎታል። ሆኖም አሁን በቀኖና መሻር ምክንያት የገጠማት ችግር ቤተ ክርስቲያኒቱ በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ የነበራትን ዓይነተኛ ሚና በእጅጉ እያቀጨጨው ይገኛል። ከሥር ከመሠረቱ ከባድ በሆነ መንፈሳዊ ጉድለት ማለትም በቀኖና መጣስ ላይ አዲስ አካሄድን መሥርቶ መጓዝ የሚያመጣውን ችግር እነሆ ዛሬ በሰፊው እያየነው ነው ።

ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያችን ችግር የሚፈታውና የአባቶች ክብር የሚመለሰው፥ አፍአዊ በሆኑ ጥቂት ስሕተቶች ላይ በማተኮርና የቤተ ክርስቲያንን ክብር በሚያዋርድ መልኩ በአደባባይ እሰጥ አገባ ውስጥ በመግባት ሳይሆን፥ ዘላቂ የሆነ መፍትሔ ሊያመጡ የሚችሉ ግልጥና እውነተኛ ውይይቶችን በማድረግ ነው ብሎ ስለሚያምን አሁን ለሠላሳኛ ጊዜ ባደረገው መደበኛ ስብሰባው ላይ በቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነትና በሌሎችም መንፈሳዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች በሰፊው በመወያየት የሚከተለውን መግለጫ አውጥቶአል።

1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ፈርሶና ሕጋዊው ቅዱስ ፓትርያርክና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ከተሰደዱበት ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን በከባድ ፈተና ውስጥ ናት ፤ ሆኖም በስደት ያሉትን ልጆቹን የማይተው ልዑል እግዚአብሔር በሰጣቸው ኃይል በስደት ላይ ያለው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያንን ክብር ለማስመለስ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ቤተክርስቲያኒቱ ወደቀድሞ ክብሯ

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የኒቫዳ አሪዞናና አይዳሆ ኤጲስ ቆጶስ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ዋና ጸሐፊ
Aba Yoseph Bishop of Nevada, Arizona, Idaho & the exiled E.O.T.C Holy Synod vice secretary

ለመመለስ እየተደረገ ባለው ጥረት ቅዱስ ሲኖዶሱ አስቦበት ስለነበር ፥ ራሱ የሰላም ኮሚቴ አዘጋጅቶ ሁኔታው በመከታተል ላይ ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ የተለያዩ ግለሰቦች በራሳቸው አነሳሺነት ባደረጉት እንቅስቃሴ የሰላም እና አንድነት ጉባኤ ብለው ሰይመው የሰላም ሂደቱ እንዲጀመር ቅዱስ ሲኖዶሱን ፈቃድ መጠየቃቸው ይታወሳል። በዚህም መሰረት ቅዱስ ሲኖዶሱ የሰላሙ ሂደት እንዲቀጥል መልካም ፈቃዱ መሆኑን ገልጾ ፥ ሆኖም ግን የሰላም ልኡካኑ በወቅቱ እንደገለጹት ፥ ከኢትዮጵያ የመጡት ልኡካን በሰላም ኮሚቴው በኩል የቀረበላቸውን ቅድመ ሁኔታ ስላላሟሉ ሂደቱ በታቀደለት መልኩ ሊቀጥል አልቻልም። ቅዱስ ሲኖዶስ ከምንም በላይ ቤተክርስቲያን ወደ ቀድሞ ክብሯ ተመልሳ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የእግዚአብሔርን ወንጌል መንግሥት እየሰበከች ለሕዝቧ የአንድነት ፣ የሰላም እና የእውቀት ማዕከል እንድትሆን ይፈልጋል። ለዚህም በትጋት ይሠራል ሆኖም አሁን ባለው የቀኖና እና የሥርዓት ቤተክርስቲያን መጣስ ምክንያት ይህንን ዓላማዋን ከግብ ማድረስ አልቻለችም። ወደፊትም ቢሆን ቀኖናዋ ተከብሮ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን እስካልተጠበቀ ድረስ ወንጌለ መንግሥትን ማሰራጨት አይቻልም ብሎ ቅዱስ ሲኖዶሱ ያምናል። ስለዚህ ፓትርያርክ እያለ በሕገ ወጥ መንገድ ፓትርያርክ መሾሙንና ቀኖና መጣሱን ማመን እስከቻሉ ድረስ የሰላም ሂደቱ እንዲቀጥል ቅዱስ ሲኖዶሱ ወስኖአል። ይህንንም ውሳኔ ሕዝበ ክርስቲያኑ በትክክል እንዲረዳውና ከስሜታዊነት በራቀ መንገድ በጸሎትና በጾም ወደ አምላኩ እንዲያመለክት ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

2. በስደት ላይ ያለችው ቤተክርስቲያን አገልግሎቱዋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ በመምጣቱ የአገልግሎቱ አሰጣጥ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲከናወን የአሠራሩን አካሄድ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል። በመሆኑም ሊቃነ ጳጳሳት በተመደቡባቸው ሀገረ ስብከቶች ሊኖር ስለሚገባው መዋቅር ፥ አዲስ በሚመደቡ እና ከቦታ ቦታ በሚዘዋወሩ እንዲሁም በሞት በተለዩ ሊቃነ ጳጳሳት ምትክ ሊቃነ ጳጳሳትን ስለ መሾም ፥ ቅዱስ ሲኖዶስ ተወያይቶአል። በመሆኑም በዋሽንግተን ዲሲ የሲኖዶሱ ጽሕፈት ቤት በሰፊው ተጠናክሮ ሥራውን እንዲቀጥል ቅዱስ ሲኖዶሱ ወስኖአል።

3. ቅዱስ ሲኖዶስ ይህችን ታሪካዊት የሆነች ቤተ ክርስቲያን ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ የሚቻልበትን መንገድ መፈለጉ ዐቢይና ተቀዳሚ ተግባሩ እንደሆነ ያምንበታል። በተለይም በውጭው ዓለም የተወለዱ ወይም በሕጻንነታቸው ካገራቸው የወጡ ታዳጊ ወጣቶች ሃይማኖታቸውንና ባህላቸውን በሚገባቸው ቋንቋ ካልተማሩ ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው እየራቁ ስለሚመጡ አፋጣኝ የሆነ መፍትሔ መፈለግ እንዳለበት ጉባኤው አምኖበታል። በመሆኑም ሕጻናትና ወጣቶችን በሚገባቸው ቋንቋ ፣ ሃይማኖታቸውንና ፣ ባሕላቸውን በተጨማሪም የሀገራቸውን ቋንቋ

AY

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የኔቫዳ የአሪዞና አይዳሆ ኤጲስ ቆጶስ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ዋና ጸሐፊ
Aba Yoseph Bishop of Nevada, Arizona, Idaho & the exiled
E.O.T.C Holy Synod vice secretary

እንዲማሩ ካህናት ከፍተኛ ኃላፊነት ስላልባቸው የተለየ ትኩረት እንዲሰጠው ቅዱስ ሲኖዶስ ያሳስባል። ይህንን ቁርጥ አላማ ከግብ ይደርስ ዘንድ ቋሚ ሥርዓተ ትምህርት እንዲቀረጽ ፣ በግል የተጀመሩ ጥረቶች ወጥነት ኖሮአቸው በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ተግባራዊ እንዲሆኑ ሥጦታ ያላቸው ወጣቶችን አሰልጥኖ በሚናገሩበት ቋንቋ የቅዳሴና የአምልኮ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ወላጆች እና ካህናት አስፈላጊውን ጥረት እንዲያደርጉ ጉባኤው አሳስቦአል።

4. በስደት ላይ ያለው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በየአቅጣጫው እያደረገ ስላለው ሐዋርያዊ ተግባር የቀረበለትን ሪፖርት ያዳመጠ ሲሆን ይህንን ሐዋርያዊ አገልግሎት በማስፋፋት ላይ ያሉትን ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና አበው ካህናትን ቅዱስ ሲኖዶስ አመስግኖአል። በመሆኑም ይህን ሐዋርያዊ ተልእኮ በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል በማሳሰብ በቅርቡም ከፍተኛ የሆነ ሐዋርያዊ ተግባር በአውሮፓ ባሉት አገሮች በሙሉ የሚንቀሳቀስ ሰባክያን ወንጌልን ያቀፈ የልዑካን ቡድን እንዲላክ ፤ የቅዱስ ሲኖዶሱ መደበኛ ጉባኤም ቅዱስ ሲኖዶሱ በወሰነው ጊዜና ቦታ ከአሜሪካ አህጉራት ውጭ የሚካሄድበትን ሁኔታ እንዲያመቻች ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኖአል።

5. በስደት ዓለም ሐዋርያዊ ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ቆይተው ባረፉት በብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ መታሰቢያነት የተመሠረተውን ገዳም የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ቅዱስ ሲኖዶስ ያዳመጠ ሲሆን ፤ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በሚመራው የገዳሙ የበላይ ኃላፊዎች አማካይነት እየተከናወነ ያለው የገንዘብ ማሰባሰቢያ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሲያሳስብ ገዳሙን ለመርዳት በህዝበ ክርስቲያኑ የታየው ታላቅ ተጋድሎ ቅዱስ ሲኖዶስን በእጅጉ ያስደሰተው ታላቅ ኦርቶዶክሳዊ ተግባር እንደሆነ በመግለጥ ጥልቅ ምስጋናውን ያቀርባል።

ማጠቃለያ

ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በስደት ላይ ያለው ሕዝባችን እና እርሱን እያገለገሉ ያሉ አበው ካህናት እያደረጉ ያሉት መንፈሳዊ ተጋድሎ ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ተስፋ እንደሆነ ያምናል። ሕዝባችን ከዕለት ጉርሱ እየነጠቀ ለቤተ ክርስቲያን ሕንፃ መሥሪያና ለአገልግሎቱ መስፋፋት እያደረገ ያለው አስተዋጽኦ ፤ አባቶች ካህናትና ሰባክያነ ወንጌልም ለግል ኑሮአቸው ምንም ሳያስቡ ሕዝበ ክርስቲያኑን በትምህርተ ወንጌል ለማነጽ የሚያደርጉትን ጥረት ቅዱስ ሲኖዶስ በማሰብ አምላካችንን ያመሰግናል።

ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ምንም እንኳ አስደሳች በሆነ ሁኔታ አገልግሎቱን እየሰጠ ያለ ቢሆንም ፤ አንድነትና ፍቅር በቤተ ክርስቲያን ቢፈጠር ኖሮ ከዚህ የበለጠ

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የኒቫዳ አሪዞናና አይዳሆ ኤጲስ ቆጶስ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ዋና ጸሐፊ
Aba Yoseph Bishop of Nevada, Arizona, Idaho & the exiled E.O.T.C Holy Synod vice secreta

ታላላቅ አገልግሎቶችን በቅድስት አገር ኢትዮጵያም ማከናወን ይቻል እንደነበረ ያምናል። ዛሬ ግን ያለው እውነታ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኦርቶዶክሳውያን እረኛ በማጣት ከሃይማኖታቸው የተናወጡበት ፥ በቤተ ክርስቲያን ያለው ሰላም የደፈረሰበት ሁኔታ ነው። በመሆኑም ለቤተ ክርስቲያን እናስባለን የሚሉ ወገኖች ሁሉ ይህ የቤተ ክርስቲያንን ህልውና ከመሠረቱ እየሸረሸረ ያለው የአንድነትና የሰላም ማጣት በአስቸኳይ መፍትሔ እንዲያገኝ ማሰብ እና በጸሎትም ወደ አምላካቸው ማመልከት እንዳለባቸው ቅዱስ ሲኖዶስ ያሳስባል። በቅድስት አገር በኢትዮጵያ ያሉ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መምህራን ፥ አባቶች ካህናትና ወንድሞች ዲያቆናት መላው ሕዝበ ክርስቲያን የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ሥርዓት የሕዝባችንም ፍጹም የሆነ አንድነት መሠረቱን እንዳይለቅ ተግተውና ነቅተው ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲጠብቁ ቅዱስ ሲኖዱሱ ጥሪውን ያቀርባል።

በመጨረሻም ላለፉት ፲፰ ዓመታት ይህንን የሲኖዶስ ጉባኤ በማስተናገድ ላይ ያሉትን የደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ካቴድራል ካህናት የሰበካ ጉባኤ አባላትና ፥ ምእመናንን ቅዱስ ሲኖዶሱ አመስግኖ ፥ በርክበ ካህናት የሚካሄደው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በካልጋሪ ካናዳ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል እንደሚደረግ በመወሰን ጉባኤውን አጠናቋል።

የቤተ ክርስቲያን አምላክ አገራችን ኢትዮጵያን አሜሪካንን ይባርክልን
ለዓለም ሰላምን ይስጥልን

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን።

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የኔቫዳ አሪዞናና አይዳሆ ኤጲስ
ቆጶስ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ዋና ጸሐፊ
Aba Yoseph Bishop of Nevada,
Arizona, Idaho & the exiled
E.O.T.C Holy Synod vice secretary